# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
## የከንቲባ ጽ/ቤት
## CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA
### Office of the Mayor

ቀን 24/12/09
Date

ቁጥር
No.

ለሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ

አዲስ አበባ፣

ጉዳዩ፡- የካቢኔ ውሣኔ እንዲፈፀም ስለማሳወቅ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ ሐምሌ 11 ቀን 2009 ዓ.ም. በ19ኛ መደበኛ ስብሰባ ያሳለፈውን ውሣኔ 8 ገጽ ፎቶ ኮፒ ቃለ-ጉባኤ በዚህ ደብዳቤ ሸኚነት እየላክን፣ በካቢኔው ውሣኔ መሠረት አስፈላጊው እንዲፈፀም እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

የከንቲባ ጽ/ቤትና
የካቢኔ ጉዳዮች ም/ኃላፊ

☎ 55 01 11 ቴሌ ፋክስ 0111 55 36 88
0111 11 06 29 ✉ 356,2445

# በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር
# ሠራተኛና ማኅበራዊ ጉዳይ ቢሮ
## Addis Ababa City Government
## Bureau of Labour & Social Affairs

ቀን: ~~10 መስከረም 2010~~
Date:

ቁጥር: 6/1/10/99/10
Ref. No:

***በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ***

***ለልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት***

***ሠ.ማ.ጉ.ቢሮ***

***ጉዳዩ፡- <u>የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ መመሪያ ቁጥር 2/2009 የካቢኔ ውሣኔ ስለማሳወቅ፤</u>***

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ከንቲባ ጽ/ቤት በቀን 24/12/09 በቁጥር አ.አ/ከ.ፅ/17/30.10/62 በላከው ደብዳቤ ***«የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ ማስተፍ አፈፃፀም መመሪያ ቁጥር 2/2009»*** በተመለከተ የአስተዳደሩ ካቢኔ ሐምሌ 11/2009 ዓ.ም በ19ኛ መደበኛ ስብሰባው ያሳለፈውን ውሣኔ 8 ገጽ ፎቶ ኮፒ በሸኝነት የላከ ሲሆን በካቢኔው ውሣኔ መሠረት አስፈላጊው እንዲፈፀም አሳስቧል፡፡

ስለሆነም በካቢኔው ውሣኔ መሠረት መመሪያውን የመጨረሻ ቅርጽ በማስያዝ ወደ ተግባር እንድትገቡና ለሚመለከታቸው አካላት ተደራሽ እንድታደርጉ እንዲሁም መመሪያውን መሠረት በማድረግ አስፈላጊው እንዲፈፀም አሳስባለሁ፡፡

ከሠላምታ ጋር

የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ
ኃላፊ

***<u>ግልባጭ/</u>***

***በአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር***

- ለከንቲባ ጽ/ቤት (ያለ አባሪ)
- ለፋይናንስ ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ (ያለ አባሪ)
- ለፍትህ ቢሮ (ያለ አባሪ)
- ለመሬት ማኔጅመንት ልማት ቢሮ (ያለ አባሪ)

***በሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ***

- ለምክትል ኃላፊ (አሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ዘርፍ)
- ለምክትል ኃላፊ (ማህበራዊ ዘርፍ)
- ለማህበራዊ ዋስትና ፈንድ ልማታዊ ሴፍቲኔት ኤጀንሲ
- ለሚከሊላንድ የማ/ልማት ማሰ/የሰው ሰራሽ አካልና የአ/ድጋፍ ማምረቻ ተቋም
- ለቃሊቲ አረጋውያን ክብካቤ ተቋም
- ለአካል ጉዳተኞች ጊዜያዊ ክብካቤ ማቋቋሚያ ተቋም
- ለአካል ጉዳተኞች ዘለቄታ ክብካቤ ተቋም
- ለአሠሪና ሠራተኛ ጉዳይ ቋሚ ቦርድ

<u>አዲስ አበባ</u>

+251 111 550244/45/ 011 1571348/011 826 3344 info.aabolsa@gmail.com Website: http://www.aabolsa/gov.et
3328 አዲስ አበባ ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

## የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ የ2009 በጀት ዓመት

## 19ኛ መደበኛ ስብሰባ ቃለ-ጉባኤ

የስብሰባ ቦታ …………… በካቢኔ መሰብሰቢያ አዳራሽ

የስብሰባው ቀን ………. ማክሰኞ ሐምሌ 11 / 2009 ዓ.ም

የስብሰባው ሰዓት……….. ከቀኑ 11:40 ሰዓት ተጀመረ

በዕለቱ ስብሰባ ላይ የተገኙ የካቢኔ አባላት

1ኛ/ ክቡር ከንቲባ አቶ ድሪባ ኩማ………………………………………………………… ሰብሳቢ

2ኛ/ አቶ ይድነቃቸው ዋለልኝ / የቤቶች ልማት አስተዳደር ቢሮ ኃላፊ /…………………… አባል

3ኛ/ አቶ ይስሃቅ ግርማይ / የፐ/ሰርቪስና የሰው ሃ/ል/ቢሮ ኃላፊ/…………………………… "

4ኛ/ አቶ ዲላሞ ኦቶሬ / የንግድ ቢሮ ኃላፊ /………………………………………………… "

5ኛ/ አቶ ዮናስ አያሌው / የኮንስትራክሽን ቢሮ ኃላፊ /………………………………………… "

6ኛ/ አቶ ልዑልሰገድ ይፍሩ / የጥቃቅንና አነ/ኢንተርፕራይዝ ልማት ቢሮ ኃላፊ/………… "

7ኛ/ አቶ ንጋቱ ዳኛቸው / ወጣቶችና ስፖርት ቢሮ ኃላፊ /…………………………………… "

8ኛ/ አቶ ኤፍሬም ግዛው / የሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ ኃላፊ /………………………… "

9ኛ/ ዶ/ር ጀማል አደም / የጤና ቢሮ ኃላፊ / ……………………………………………… "

10ኛ/ አቶ ጀማል ረዲ / የኢንዱስትሪ ልማት ቢሮ ኃላፊ /……………………………………… "

11ኛ/ አቶ ሰዓለም ብርሃኑ / የፕላን ኮሚሽን ም/ቢሮ ኃላፊ /………………………………… "

12ኛ/ አቶ ሙሉነህ ወርዶፋ / የፍትህ ም/ቢሮ ኃላፊ /…………………………………………… "

13ኛ/ አቶ መሣይ ደምሴ / የባህልና ቱሪዝም ም/ቢሮ ኃላፊ / ………………………………… "

14ኛ/ ወ/ሮ ስንታየሁ ማሞ / የሴቶችና ህፃናት ጉዳይ ም/ቢሮ ኃላፊ /………………………… "

15ኛ/ አቶ ነስረዲን መሐመድ / የኮሙኒኬሽን ጉዳዮች ም/ቢሮ ኃላፊ / …………………… "

ከስብሰባው ተሳታፊ

1ኛ/ አቶ አሰግድ ጌታቸው ……………………… የከንቲባ ጽ/ቤትና ካቢኔ ጉዳዮች ኃላፊ

2ኛ/ ወ/ሮ ቆንጅት ደበላ ………………………………… ም/ሥራ አስኪያጅ

ስብሰባው ላይ ያልተገኙ

ኛ/ ክቡር ምክትል ከንቲባ አቶ አባተ ስጦታው ............................ በሌላ ሥራ ምክንያት

ኛ/ አቶ ለዓለም ተሠራ / የመሬት ልማትና ማኔጅመንት ቢሮ ኃላፊ /......... " " "

ኛ/ አቶ መሀመድ አህመዲን / የትምህርት ቢሮ ኃላፊ /......................... " " "

ኛ/ አቶ ፎኢኖ ፎላ / የፋይናንስና ኢኮኖሚ ልማት ቢሮ ኃላፊ /................. " " "

ኛ/ ዶ/ር ሰለሞን ኪዳኔ / የመንገድ ትራንስፖርት ቢሮ ኃላፊ /................. " " "

ኛ/ አቶ ዘርኡ ሱሙር / የቴክኒክና ሙያ ትምህርትና ሥልጠና ቢሮ ኃላፊ / ... " " "

**ቃለ-ጉባኤ ያዥ**

ፈለቀ ነጋሽ ............................ የካቢኔ ጉዳዮች ዳይሬክቶሬት ኃላፊ

**በአቅራቢነት የቀረቡ**

1ኛ/ አቶ አሰፋ መብራቴ .................. / የሠ/ማ/ገ/ቢሮ ጽ/ቤት ኃላፊ /

2ኛ/ አቶ ኩርኩራ ዋሮ ... /በሠ/ማ/ገ/ ቢሮ የል/ተ/አ/መ/ማ/ፕሮጀክት ጽ/ቤት ዋ/ሥራ አስኪያጅ/

3ኛ/ አቶ ጌታቸው በላይ ..... /የሠ/ማ/ገ/ቢሮ የል/ተ/አ/መ/ማ/ፕሮጀክት ጽ/ቤት ም/ሥራ አስኪያጅ/

**በዕለቱ የቀረበ አጀንዳ**

የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ ማዕቀፍ አፈፃፀም መመሪያ

አጀንዳ ቁጥር .2 **የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ድጋፍ መዕቀፍ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 2/2009 ረቂቅ**

የከተማዋን ዕድገት ለማፋጠን ሲባል በሚደረገው የልማት እንቅስቃሴ ምክንያት በልማት ማስፋፊያ አካባቢዎች ውስጥ የሚኖሩ አርሶ አደሮች ከይዞታቸው እንዲነሱ እየተደረገ የቆየ በመሆኑ እና ወደፊትም ከይዞታቸው የሚሉ ስለሆነ ከይዞታቸው የተነሱና የሚነሱ ዜጎች ላይ የሚፈጠረውን መፈናቀልና ልዩ ልዩ ችግሮችን በቅድሚያ ለመከላከልና ለኢኮኖሚያዊ እና ማህበራዊ ችግር ተጋላጭ በመሆኑ የደረሰባቸውንና የሚደርስባቸውን የመልካም አስተዳደር ችግር በመቅረፍ በዘላቂነት ማቋቋም በማስፈለጉ፣

የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ካቢኔ በተሻሻለው የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ቻርተር አዋጅ ቁጥር 361/1995 በተሰጠው የህግ ስልጣን መሠረት የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የልማት

ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት በደንብ ቁጥር 79/2008 ዓ.ም እንዲቋቋም እንደተደረገ፣

ይህ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ከተቋቋመ በኋላ በደንቡ ላይ የተገለጸውን ዓላማ እና የተሰጠውን ስልጣንና ተግባር መነሻ በማድረግ በመዋቅራዊ አደረጃጀቱ መሠረት የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ተጠቃሚ መሆን ያለባቸውን በልማት ምክንያት ከይዞታቸው የተነሱትን መልሶ ማቋቋም እና በቀጣይም የሚነሱ አርሶ አደሮችን ከኢኮኖሚያዊ ማህበራዊ ችግር ለመከላከል እና የኑሮ ሁኔታቸው እንዲሻሻል ለማድረግ በቅድሚያ የፕሮጀክቱ ተጠቃሚዎችን ከኪራይ ሰብሳቢነት፣ ከመልካም አስተዳደር ችግሮች እንዳይጋለጡ እንዲሁም ፍትሃዊነት፣ ግልጽነትና ተጠያቂነት ባሰፈነ መልኩ በድጋፍ መስፈርቶች፣ በድጋፍ አፈጻጸም ሂደቶች እና የድጋፍ ስርዓቶች አስመልክቶ ግልጽ በሆነ መመሪያና አሰራር መፈጸም ስላለባቸው ይህን የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ የድጋፍ አፈጻጸም መመሪያ ማዘጋጀት እንዳስፈለገ፣

በመሆኑም የአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር ሠራተኛና ማህበራዊ ጉዳይ ቢሮ በልማት ተነሺ አርሶ አደሮች መልሶ ማቋቋሚያ ፕሮጀክት ጽ/ቤት ማቋቋሚያ ደንብ ቁጥር 79/2008 ዓ.ም መሠረት ይህን መመሪያ እንደወጣ በፅሑፍ ተብራርቷል።

<u>በውይይቱ ወቅት በካቢኔ አባላት ከተነሱት አስተያየቶችና ጥያቄዎች ዋና ዋናዎቹ</u>

- ምንም ገቢ የሌላቸውና መስራት የማይችሉ በምን መነሻ ተለየ ምንም ገቢ የሌላቸው ግን መስራት የሚችሉ ምን ማለት ነው? ዝቅተኛ ገቢ አላቸው ሲባል እስከ ምን ከፍተኛ ገቢ ያላቸው በምን ተለየ?
- የትራንስፖርት ብር ለምን አስፈለገ ት/ቤት፣ ጤና ጣቢያ መንግስት ነው የሚገነባው የትራንስፖርት ገንዘቡ ለምን ይሰጣል?
- የአንዳንድ ቦታ ቦርድ ወይም የከተማው አስተዳደር ወይም ቢሮው ይላል የኃላፊነት ግጭት ስለሚፈጥር የህግ ሰነድ ስለሆነ የከተማው አስተዳደር ወይም ቦርዱ ቢለይ፣
- ምንም ገቢ የሌላቸውን አካላት መስራት ለማይችሉ እስከ መቼ ነው የሚደጎሙት መስራት አይችሉም ከተባለ ግልፅ መደረግ እንዳለበት፣ ጡረታ ዘመን በሙሉ እንዴት ይታገዛሉ ጥገኝነት እንዳይመጣ ቢታሰብበት፣
- መሥራት የሚችሉ 2840 ሰዎች የተባለው እንዴት ተለዩ፣

- በአካውንታቸው በየ6 ወር ይገባል ይላል በአድሜ ገደብ አልተቀመጠም ለብክንት ይጋለጣል፣ እነሱን ለማቋቋም፣ ግብአት የምናቀርብለትና የሥራ ዕድል ፈጠራ ከሆነ ብድር የምናመቻችለት ከሆነ ለምን 6 ወር ይጠበቃል?
- ቤተሰብ የሚለውን በደንብ ካላስቀመጥን እየሰፋ ሊሄድ ስለሚችል ለአፈፃፀም እንዳያስቸግር ግልፅ ቢደረግ፣
- የመኖሪያ ቤት ድጋፍ የሚለው የቀበሌ ቤት እየፈረሰ ስለሆነ ለልማት ተነሺ አርሶ አደሮች እንደ አማራጭ መመሪያ ውስጥ መግባት የለበትም፣ የከተማ አስተዳደሩ በተመጣጣኝ ዋጋ ቤት ማስገንባት አለበት በተመጣጣኝ ዋጋ በኪራይ እናስተላልፋለን ከሆን ታስቦበትና ተወስኖ እዚህ ወስጥ መግባት ያለበት  ስለዚህ ከቀበሌ ቤት ጋር ተያይዞ ያለው ቢወጣ፣
- የድጋፍ ማብቂያ ጊዜ ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ማብቂያ ጊዜ ጋር የሚያስቸግር ስለሚሆን ከፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ህልውና ጋር ማክሰም ጋር ቢታይ፣
- ልዩ ተጠቃሚነት ጋር እንዴት ይያያዛል? የካሣ ክፍያ ወደ ኋላ በመጠየቅ የሚያነሷቸው ጥያቄዎች ስላሉ ቢታይ፣
- ለዝቅተኛ 50 ፐርሰንት ፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ለመካከለኛ ከፍተኛ ገቢ ለሌለውም ቢለይ፣ ለሁሉም ተመሳሳይ ከሆነ ምንም ገቢ ለሌለውና ዝቅተኛ ገቢ ላለው እስከመካከለኛ ድረስ ሊሄድ ስለሚችል ከፍተኛ ደረጃ ላለው ብናይ፣
- ከዚህ በኋላ ለሚነሱት በዘላቂነት ፕሮጀክት መቅረፅ የሚለው  ከዚህ በኋላ ለሚነሱት አካላት የታሰበው ምንድነው?
- ቦታ በድርድር የሚለው እዚህ መመሪያ ውስጥ ባናስገባው  የመሬት አሰጣጥ ራሱን የቻለ መመሪያ ስላለ በዚያ ቢታይ
- በቅድሚያ የማልማት መብት የሚለው ጥያቄ እንዳያስነሳ በአርሶ አደሩ አቅም የሚለማ ከሆነ መሬቱ ለምን አርሶአደሩ ይነሳል ማብራሪያ ቢሰጠው፣
- የእማወራዎች በልዩ ተጠቃሚ የሚሆኑበት ታይቷል ወይ?
- ዘላቂ ማቋቋም ላይ በከተማ አስተዳደሩ ሆስፒታሎች እስከሚቋቋሙ የነፃ ህክምና ፣ ልጆቻቸው በነፃ ትምህርት ቤት የማስተማር ነፃ የአውቶብስ አገልግሎት ተጠቃሚ እንዲሆኑ  በመመሪያው ላይ በግልፅ ቢቀመጥ፣
- 4 ዓመት ራሳቸውን ችለው ብድር ይመልሳሉ የሚለው ቢታይ፣

- ለህዘብ ጥቅም ስለሆነ መሬታቸውን የለቀቁ የአርሶአ. [illegible]
  በተቻለ መጠን ቢደረግ፣
- ለምልመላ ኮሚቴ ቅርንጫፍ ጽ/ቤት እንዳለ ያሳያል በአመራር እንዲመራ ቢደረግ፣
- ቅሬታ ማቅረቢያ ጊዜ ጋር አምስት ቀናት የሚለው የአርሶአደር የኑሮ ሁኔታ ከምንሠራው ዘለቄታ ሥራ ጋር ዝቅተኛ ስለሚሆን ታሳቢ ቢደረግ፣
- የቅሬታ ስርዓት መዘርጋት የለብንም ወይ?
- ምንም ገቢ የሌላቸውና መስራት የማይችሉ የሚለው ማንን ነው የሚመለከተው?
- የአልባሳት እና የምግብ ብር1600.00 ሲባል አባወራውን ብቻ ወይስ በሥሩ ያሉ ህፃት ልጆችን ያካትታል እንዴት ነው የሚታዩት የልጅ ብዛት ስለሚኖር ግልፅ ቢደረግ፣
- የማቋቋም ፕሮግራም ላይ ከፍተኛና መካከለኛ ገቢ ያለው በሁለቱ መሃል ልዩነት ስላለው መለየት እንዳለበት፣
- የመስሪያ ቦታ ሳይሆን ሼድ በሚል በዛ ደረጃ ቢያዝ አይሻልም ወይ?
- ይሄ ድጋፍ እስከመቼና ጤንነታቸው ተስተከክሎ ወደ ሥራ ይሰማራሉ?
- ልዩ ልዩ ድጋፍ ጋር ተያይዞ የትራንስፖርት ምልልሱ ምን ያህል ወደ ታአማኒነት የቀረበ ነው የሚለው ቢታይ፣
- ቅድሚያ የማልማቱ ጥሩ ሆኖ አርሶአደሮችን አንድ ላይ ተደራጅተው ፎቅ ሰርተው እንዲጠቀሙ እንዲደረግ ከመሬት ልማት ጋር በደንብ ተነጋግሮ ቢቀመጥ አይሻልም ወይ?
- ቅድሚያ የማልማት መብትን በተመለከተ በቀጣይ አርሶ አደሮች ሲነሱ ቦታው ላይ ስታንዳርድ ሊኖረው ይገባል እዚያው አካባቢ ወይም ፕላኑን በጠበቀ መልኩ የሚያስሙበት መልኩ ቢኖር፣
- የአዲስ አበባ ዙሪያ እንደተሞክሮ ይወሰዳል ከተባለ ሃብት እንዳለ ሳይሆን ችግር ፈቺ በሆነ መልኩ ቢሆን የተሻለ እንደሚሆን አስተያየት ቀርቧል፡፡

<u>የአቅራቢውና የካቢኔ አባላት አስተያየት / ምላሽ /</u>

- የመረጃ እይታ የተጠናቀቀ ሥራ እንዳልሆነ፣ ፕሮጀክቱ ከመቋቋም በፊት ከተቋቋመ በኋላ የመሬት ልማት ማኔጅመንት ቢሮና ፋይናንስ ቢሮ የፋይናንስ ስርዓቱ እንዴት ነበር ብሎ ለማየት እየተደራጀ ያለ መረጃ ከሞላ ጎደል ከመንግስት ቋቋማት የተገኘ እንደሆነ፣



Addis Ababa City Government Labour & Social Affairs Bureau

0111 11 06 29 356,2445

- መረጃ የታአማኒነትን በተመለከተ አርሶአደርና ተወካዮቻቸው የሚያነሱት በርካታ መረጃዎች ቢኖሩም የቀረበውን መረጃ ሁሉ እንደመረጃ እንዳልተወሰደ፣
- ቦሌ ለሚ ኢንዱስትሪ ልማት፣ ዓለም ባንክ፣ ሲቪል ሰርቪስ ዩኒቨርስቲና ከፖሊሲ ጥናት ምርምር ያጠናቸው ጥናቶች ለመረጃነት እንደዋሉ፣ አሁንም መረጃዎችን ለማሰባሰብ ጥረት እተደረገ እንደሆነ፣
- ግልፅ ይደረጉ ተብለው የቀረቡ አስተያየቶችን የተባሉትን እንደሚወሰዱ፣ ሆኖም ብዙ አከራካሪ ጉዳዮች እንዳሉ ታሳቢ እንዲደረግ፣
- ዝቅተኛ መካከለኛ ከፍተኛ ገቢ ተብሎ የተለየውን በተመለከተ ግልፅ እንደሚደረግ፣ የቤተሰብን ትርጉም በተመለከተ በሀገሪቱ ህግ መሰረት ያለውን ትርጉም ይዞ እንደሚደረግ፣
- አስተዳደሩ ቦርዱ የሚለው አንዳንድ ጊዜ ጠቃሚ ስለሚሆን ለሌላው ክፍተት ለመስጠት ስለሆነ ከፍትህ ቢሮ ጋር ከህግ አኳያ በጋራ እንደሚታይ፣
- ከተጠቃሚነት አኳያ ከፍ ማድረግ ያለበትን ከፍ በማድረግ ዝቅ ማድረግ ያለበትን ዝቅ በማድረግ ከዚህ እስከዚህ የሚለው እንደሚቀመጥ፣
- ቦታ ሳይሆን ሼድ ነው መስጠት ያለበት የሚለው ትክክል እንዳልሆነና ለአርሶ አደሩ በተለየ መንገድ እንዴት እናስተናግደው መሆን እንዳለበት፣ የፌዴራል ጉዳዮች ክልዩ መብት ተጠቃሚት ከሚያነሳቸው አንዱ የአርሶ አደር ስለሆነ የአርሶ አደር ጥያቄ ይመለስ ሲባል በልዩ ሁኔታ መመለስ ያለበትና ቦታ ሲባል የሚወስነው ካቢኔው እንደሆነ፣
- የመኖሪያ ቤትን በተመለከተ ምንም አማራጭ የሌላቸው የቀበሌ ቤት የተባለው ትክክል እንዳልሆነ፣ በልዩ ሁኔታ ታይቶ በግንባታ ቦርዱ እንደሚወሰን ከቤቶች ልማትና ከኮንስትራክሽን ጋር በጋራ ቢፈፀም የተሻለ እንደሚሆን፣
- እማወራዎችን በተመለከተ እንደሚወሰድ፣
- ቅድሚያ የማልማት ጉዳይ ላይ አሠራር ስላለው እንደ ፕሮጀክት ጽ/ቤት አንደኛው ከቅድሚያ ማልማቱ ጋር ብዙ የማይያያዝ ለምሣሌ ብልማት ምክንያት የሚነሱ ሰዎች አሉ ለሚነሱ ሰዎች በህጉ መሠረት ለ20 ሰዎች ለእያንዳንዱ 500 ካሬ ሜትር አጠቃላይ 10000 ካሬ ሜትር ይሰጣቸዋል፣ ይህ በህግ የተሰጣቸው መብት ስለሆነ እነኝህን ሰዎች በማወያየትና በማደራጀት አንድ ቦታ እንዲወስዱ በማድረግ ካሳ ማሻሻያን ተጠብቆለት የተሻለ ቦታ ተሰጥቷቸው በአክስዮን ተደራጅተው የላቀ ተጠቃሚ እንዲሆኑ

ለማድረግ ከማስተር ፕላኑ ጋር በማይጋጭበት ሁኔታ የሚያለሙበት መንገድ እንዲመቻች ስለሆነ አንዳንዱ የሚነሳው ቦታ በተበጣጠሰ መንገድ በሚሰጥበት ወቅት የማልማት አቅማቸው በብድር በማመቻቸት በአክስዮን በማደራጀት ከባንክ ጋር ማስተሳሰርና ተጠቃሚ ማድረግ፣

- ከፍተኛና መካከለኛ የከተማ ግብርና ሥራዎች ስላሉ ከንግድ ቢሮ ጋር በመነጋገር በከተማ ግብርና ትኩረት በማድረግ የተለየ ትኩረት ተሰጥቶት የማቀናጀት ሥራ መሠራት እንዳለበት፣
- ከኪራይ ሰብሳቢነት አንፃር ቦርድ ስላለ ሥራውን ይገመግማል የህግ ማዕቀፍ ስለተዘጋጀ ኪራይ ሰብሳቢነትን እንደሚቀንስ፣
- የፕሮጀክት ጽ/ቤቱ ሥልጣንና ኃላፊነት ከማሻሻል አኳር በቀጣይ ለካቢኔ ቀርቦ ውይይት እንደሚደረግበት፣
- የገቢ ደረጃ በምን ይለያል? በምዝገባ ማን ማን ይሳተፋል? የሚለው የወረዳው ነዋሪናዎች እንደሚሳተፉበት፣ የሚለይበት ሁኔታ ከራሱ ከአርሶ አደሩ ማን ምን ፕሮጀክት ላይ እንደሚጠቀም የሚለይበት አሠራር ሊኖር እንደሚችል፣
- ምንም ገቢ የሌለው እና መሥራት የማይችለውን በማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ መረጃ መሠረት መነሻ እንደሚደረግ፣
- መሥራት የማይችሉ ተብሎ የተገለፀው ባለባቸው የአካል ጉዳት የእድሜ የጤና እክል ምክንያት በማንኛውም የሥራ መስክ ሊሰማሩ የማይችሉእና በዘላቂነት ድጋፍ የሚደረግላቸው አርሶ አደሮችን ለማመላከት እንደሆነ፣
- በአርሶ አደሩ ስም የሚገኙ ጥገኞችን እንዴት እንከላከላለን የሚለውን ሙሉ በሙሉ ለማስወገድ ከባድ ቢሆንም የአሠራር ማንዋል በማውጣት ለመከላከል ጥረት እንደሚደረግ፣
- መመሪው ሳይፀድቅድ ተግባራዊ ማድረግ አስቸጋሪ ስለሆነ መመሪያው ፀድቆ ቶሎ ወደ ተግባር እንድንገባ ቢደረግ፣
- የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ከመቼ ጀምሮ ተጠቃሚ ይሁኑ የሚለው ባለመወሰኑ ምክንያት መረጃ ለመሰብሰብ አስቸጋሪ ስለሆነ ከኦሮሚያ ክልላዊ መንግስት ተሞክሮ ሲወሰድ ከ1986 እንደሆነ፣ ከአርሶ አደሮች ጋር በተደረገ ውይይትም የአየር መንገድ ማስፋፊያ ጋር ተነሺዎቹ ከ1986 ጀምሮ እንደነበረ እና የሊዝ ህጉም በስፋት ተግባራዊ የሆነው ዓ.ም ስለሆነ እንደመነሻ እንደተወሰደ፣

7

- የይዞታ ማረጋገጫ በተመለከተ ከክልሎች ተሞክሮ ተወስዶ እንደነበርና ክልሎች ለአርሶ አደር የይዞታ ማረጋገጫ ካርታ ይሰጣሉ በልማት ሲነሳ ያለክርክር ቦታውን አስረክቦ ይሄዳል ይዞታውም ይታወቃል አዲስ አበባ እንዳልተጀመረ፣ ጥቅሙም አንዳንዶቹ በህገ-ወጥ መንገድ መሬት ስለሚሸጡ የይዞታ ማረጋገጫ ቢኖር ህገ-ወጥ ግንባታውን መቆጣጠር እንደሚቻል እና በተደጋጋሚም አርሶ አደሮቹም ይህን ጥያቄ ስለሚያነሱ አሁን ምለሽ ቢያገኙ የመልካም አስተዳደር ችግሩን በቀላሉ መፍታት ያስችልል።

<u>የካቢኔው ውሳኔ</u>

- ሼድ ከሚባል ግሪን ሃውስ ተብሎ ለእርሻ የሚሆኑ ግሪን ሀውሶች ስላሉ በአጭር ጊዜ ባለሀብት የሚሆንበት መንገድ እንዲመቻች፣
- ትምህርት ቤት የተባለው ወጪውን ጨምሮ ለተማሪ ለብቻ ተብሎ ከሚሰይ ልጆቹን ለማስተማር ተብሎ ቢመጣ አሳማኝ ስለሚሆን የትምህርት ቤት እና የትራስፖርት እንደ ፓኬጅ አምስት፣ ሦስት፣ አንድ ቤተሰብ ያለው ተብሎ ተለይቶ በአንድ ፓኬጅ ተሰጥቶት ራሱ እንዲያስተዳደር እንዲደረግ፣
- በዚህ ፕሮጀክት ተጠቃሚ የሚሆኑት የልማት ተነሺ አርሶ አደሮች ከ1986 ዓ.ም. ጀምሮ ተግባራዊ እንዲሆን፣ ሌሎች በካቢኔ አባላት የተሰጡትን አስተያየቶች ታክሎበትና ዳብሮ ደንቡ እንዲፀድቅ ካቢኔው ወስኗል።

በዚህም ስብሰባው ከምሽቱ 02:30 ሰዓት ተጠናቋል።

CITY GOVERNMENT OF ADDIS ABABA

Addis Ababa City Government
Labour & Social Affairs Bureau